አንድ፣አምላክ፡በሚሆን፡በአ
ብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡
ስም፡የጻፋት፤የጴጥሮስ፡መ
ጀመሪያ፡መልእክት፣ይህች
ናት። ምዕራፍ፡፩። ክፍል፡፩።

በቃሉ፣ስብከት፡ላመኑ፣በእስጢፋኖስ፡ሞ
ት፡ለተበተኑ፣በየሀገሩ፡ላሉ፣ምእመናን፡
ቅዱስ፡ጴጥሮስ፡የሥጋዊውንና፡የመንግ
ሥት፣ሰማያትን፡ነገር፡እንደ፡ጻፈላቸው

፩ ከጌታችን፡ከኢየሱስ፡ክርስቶ
ስ፡ሐዋርያ፡ከጴጥሮስ፡የተላከች
መልእክት፡ጳንጦስና፡ገላትያ
ቀጰዶቅያና፡እስያ፡ቢታንያ
ም፡በተባሉ፡አገሮች፡ላሉ፡ለተ
መረጡም፡ሰዎች፡ትድረስ። ያ
፪ ዕ፡፩፡፩። በመንፈስ፡ቅዱስ፡እግ
ዚአብሔር፡አብ፡ማወቅን፡ለ
ቀደሙ፡ትድረስ። የኢየሱስ፡ክር
ስቶስን፡የደሙን፡መፍሰስ፡ይ
መሰክሩ፡ዘንድ፡ሞገስና፡ሰላ
ም፡ይብዛላችሁ። ሮሜ፡፰፡፳፱
፫ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከ
ሙታን፡በመነሣቱ፡ሕይወት፡
በምናገኝባት፡ተስፋ፡በቸርነ
ቱ፡ብዛት፡የወለደን፡የጌታችን
የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አባት፡እ
ግዚአብሔር፡ይመስገን። ፪ቆ
፬ ሮ፡፩፡፬። የማይጠፋውን፡የማይ
ለወጥና፡የማያልፈውን፡ለኛና፡
ለናንተ፡በሰማይ፡የተጠበቀ
ውን፡ለመውረስ። ቆላ፡፩፡፲፪።
፭ በኋላ፡ዘመን፡ትገለጥ፡ዘንድ፡በ
ተዘጋጀች፡መድኃኒት፡በእግዚ
አብሔር፡ኃይል፡በሃይማኖ
ት፡የተጠበቃችሁ፡ናችሁና፡ዮ
ሐ፡፲፡፳፰፡፲፯፡፲፩።
፮ ለዘላለሙ፡ደስ፡ይላችኋል፡ነ
ገር፡ግን፡ስለሚመጣባችሁ፡ል
ዩ፡ልዩ፡መከራ፡ዛሬ፡ጥቂት፡ታ
ዝኑ፡ዘንድ፡አላችኋለሁ። ሮሜ
፭፡፪፡፪ቆሮ፡፬፡፲፯፡ምዕ፡፭፡፲፩
፯ በእሳት፡ከፈተኑት፡ከጠራ፡ወ
ርቅ፡ይልቅ፡ከሚወደድ፡ሃይ
ማኖታችሁ፡መፈተኛ፡ሊሆን፡
ደግሞ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በተ
ገለጠ፡ጊዜ፡በምስጋና፡በክብ
ር፡በብርሃንም፡ትገኙ፡ዘንድ፡
አላችሁ። ም፲፪፡፫፡ሚልክ፫
፰ ፫። ሳታዩት፡የምትወዱት፡እ
ሱ፡ነው። እስከ፡ዛሬ፡ገና፡አላያ
ችሁትም፡ታምኑበታላችሁ፡
እንጂ። አሁንም፡ፍጻሜ፡በሌ
ላት፡ደስታ፡ደስ፡ይላችኋል፡ዮ
ሐ፡፳፡፳፱፡፩ቆሮ፡፫፡፪።
፱ በሃይማኖታችሁም፡ፍጻሜ፡

